# ኢትዮጵያን ዳግም ወዴት ? አፍራሹ ማነው ?

ዮሴፍ፡ አሰፋ*

ኢትዮጵያን የዲሞክራሲ ስራአት የሰፈነባት አገር እንድትሆን ለዘመናት ሲካሄድ የነበረዉና እተካሄደ ያለው የህዝብ ትግልና መሰዋእትነት በተለያየ ወቅት ትግሉን በግርግሩ መጥለፍ በቻሉ ቡድኖች እጅ ሲወድቅ ታይተዋል፤፤እነዚህ ቡድኖች የህዝቡንም ራእይ ሲያከስሙና አምባገነናዊና አጥፊ ተልእኮአቸዉን ባገርና በህዝብ ለይ ሲፈፅሙ ተስተዉለዋል።ከነመንግስቱ ንዋይ ጥያቄ ካዔው ስርአት መዉረድና ከደርግ መቆናጠጥ እስከ ወያኔ ሰረጎ ገባዊ መንግስት ምስረታ ከዚያም የግንቦቱ ምርጫ ሂደቶች ይህንን እዉነታ የሚያመላክቱ ተመክሮዎች ናቸው።ይህ ሂደት አሁንም ሊከሰትና ሊደገም የሚችልበት ሁናቴ ዉስጥ ወደ መግበት አዝማሚያ ላይ ነን።ይህንንም የሚጠቅቁሙ ፖለቲካዊ ክስተቶች በመታየት ላይ ናቸው።የወያኔው እድሜ ከቀን ወደ ቀን እያጠረ መሆኑን ሁሉም እያሸተተው ነው።ይህንንም ዋጅቶ የግንቦቱነ ምርጫ ዉጤትን ገሸሽ በማድረግ በኮንፍረንስና ከህዘብ ድምፅ በራቀ አጀንዳ የአገርና የህዝብን ብሄራዊ ጥቅምና ልእልናን ባደራደረ መልኩ የፖልቲካና የህዝብ ስልጣን ጠለፋው በግልፅ እየተመከረበት ነው።

የስልጣን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን አሁንም እንደ ወያኔ ዳግም አገር ብተናና ለሻብያ ኣሽንጉሊትነቱ እየተገፋበት ነው።ወራቶች እንዳለፉት የሚታወቀው ትብብር ለነፃነትና ለዲሞክራሲ(ትነዲ) ምስረታም በዚሁ እይታ ዉስጥ እየገባ ነው።ከምስረታው ደቂቃ አንስቶ ትነዲ ብዙ ትምህርቶችን እየሰጠ ምንነቶችን ግልጥልጥ አድርጎ እየከሰመም እየተወራጨም በዋናነት ይህንኑ እያሳየን አለ።

ሻበያዎችም ከኛ ላሳር የኢትዮጵያ አንድነትና ዘላቂ ጥቅም ጠባቂ ባዮች ሆነው ጦር አደራጅተው በገሃድ ለቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነትና አንድነት ያስፈልጋል እያሉ ያዙኝ ልቀቁኝን ገብተውበታል። ይህንንም ተከትለው ሻብያን አትነኩ ባዩ መፈልፈል ከጀመረ ሰንበትበት እያለ ነው። በዚህም አላበቃም የስልጣንና የገንዘብ ፈላጊዎች ጉዳይ እንዳለ ሆኖ የፖለቲካ ተስፋ መቁረጥና መወናበድ በነዚህ ታሪካዊ የኢትዮጵያችንና የብልፅግናችን እነዲሁም የአነድነታችን በሽታዎችና ፀሮቸ ጉያ ዉስጥ የገቡት ጉዳያ ጉድ የሚያስኝ ነው። ይታያችሁ ሻብያ የኢትዮጵያን አንድነት ብልፅግናና  ሰላም በመመኘት እራእይ ሰጥቶን ፍልስፍና አሰጨብጦን ጠመንጃ አስታጥቆን አዲስቱዋን እትዮጵያ ሲቸረን፤፡ ሻብያ እነወያኔንና ኦነግን ቹ እያለ ባቅምና በቲዎሪ እያጨናነቃቸው የኢትዮጵያን ድክመትና ዉድቀት ሲያስፈጽማቸው ቆይቶ በመጨረሻም ቻርተር ከዚያም ሻብያዊ ህገመንግስት አስፀድቆና አስፍኖ መቀመጫዉን እንዳመቻች እዉነ ነው። የግዛት ልእልና የባህር በርና ወደብ ጥያቄ እንዳይነሳ አነድነታችንን ለማናጋት በዘር በክልል በቋንቋ ከፋፍሎን ይሄው የምናየው አዘቀጥ ዉስጥ ገብተናል። ለመዉጣትም ትንቅነቅ ላይ ነን። የተለየ ችሮታ አሁንም ከሻብያ መጠበቅ የባሰ አዘቅጥ ዉስጥ ለመዘፈቅ ብቻ፡ነው። ሰታቹቱን/ትነዲን የመፀወተንም ለዚሁ ነው።

ሻብያ ከመረብ ምላሽ ገባሪ ህዝብ አገልጋይ መንግስት ታማኝ ጎረቤት አገር ወይም አገሮች ጠፍጥፎ ማስቀመጥ ከፍጥረቱ ጀምሮ የነበረው ትልሙ ነው፤፡ ለዚህም ሰተራቴጂክ ድጋፉን ለተለያዩ ድርጅቶች ሲሰጥ ቆይትዋል እየሰጠም ነው። በ1991 ከወያኔና ኦነግ ጋር ይህንን ፍላጎቱን አሰፈፅሞ እርፍ እንዳለ ነበር የሚለፈልፈው። የመቶ አመት የቤት ስራም እንደሰጠን ነግሮናል።በቅርቡ ግን ትልቅ ክስተት በግንቦቱ ምርጫ ተስታኮ ድቅን አለ። አንድ እዉነትን ገለጠ። ሻቢያ እንዳሰበው ህልሙ በዘላቂነት እዉን እንደማይሆነ ተረዳ።የግንቦቱ 1997 ምርጫ ለወያኔ ብቻ ሳይሆነ ለሻብያም ትልቅ ትምህርት ነው የሰጠው።አዉነትም በርግጥም የኢትዮጵያ ህዝብ አልተከፋፈለም። አሁንም ላንድነቱ ቀናኢ ነው። የወደብ የግዛትና የባህር በር ጥያቄዉን አላነሳም። ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ምስረታ የጠነከረ እምነት አለው።በቋንቋና በክልልም መከፋፈሉ እንደተሸረበዉና እንደተዶለተው አይደለም።የቀረፀልን ህገመንግስትም የታሰበዉን አላደረሰም ።

ለዚህ ነው ሻብያ አገራችንን አንድ ደረጃ ወደታች በሌላ አጀነዳ ማዉረድ መገፋትና ማሳነስ የፈለገው።ሻበያ ይሄው እኛን በተለያዩ ብሄረሰቦች የመገንጠል ጥያቄ አባዜ ዉስጥ ከቶ እያደናገረን ነው።ለዚህም እንቅፋት የሚሆኑትን ባንድነትና በፀረ ወያኔ አጀንዳ ደልሎ ለጥፋቱ መሳሪያ አድረጎ ኢትዮጵያን ወደማያባራ ጦርነት ዉስጥና መከፋፈል ወይም የመበተን እጣ ዉስጥ ከቶ ማስቀመጥ በሎ የሚዉተረተረው።ለዚህም ነው ትነዲ ለሻብያ የዚህ አጀንዳው ማስፈፀሚያ መሳሪያው ስለሆነ ፈጥሮት ደግፎት ለማራመድ በየቦታው ዉርዉር የሚለው።ለጊዜው ተሳከቶለት ሻብያን አትነኩ የሚለው አቀንቃኝና ቃኝ በየመንደሩ እየተፈለፈለ ህዝቡን ግራ ለማጋባት እየተሞከረ ነው።ይህ ትልቅ አደጋ ነው።ምክንያቱም ያሁኖቹ የሿብያ ካደሬዎች እንደቀድሞው ወያኔዎች ኦነጎች ሳይሆኑ ዘመን ተገልብጠ አገራዊ አጀንዳ አለን የሚሉትም ናቸው፡፡

ነገርን ነገር ያመጣዋልና በነገራችን ላይ ሻብያ አሁን ከየቦታው ሰብስቦ አንዱን ከቅኝ ግዛት ነጻ አዉጭ ሌላዉን የአንድነት ተቆርቋሪ እያለ ሞቅሞቅ እያደረገው ነው።ሁለቱንም የተራራቀ ጎራ እያጠናከረ ለየግል ፕሮግራማቸው መፈጸም በርቱ ግፉ እያላቸው ነው። ትነዲንም ፕሮግራማችሁን አትለዉጡ አታቀራርቡ ባይ ነው።ይህ ታዲያ ትልቅ አደጋ አይደለም የሚል ማን ነው? ይህ ደባ መገታትና መቆም አለበት የማይል ከአገራችን ፀር በስተቀር ማነው? ሻብያ ጉያ እስከተቆየ ድረስ ጉዳዩንና ፍላጎቱን መፈፀም የሚጠበቅና ግድ ነው።እንደ ወያኔዎቹ።ፍራቻዬ አንድቀን ጉዳዩ አልፈጸም ካለው እንደለመድው ሰብስቦ የቁምና የወይኒ እስረኛ አድርጎ እሱም በበኩሉ እንደ ልጁ ወያኔ ፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ትግል ዉስጥ እንዳይዘፍቀን ነው። እነ ቅንጅት አለም አቀፍ ጠንቀቅ ቢሉ ይሻላል።ብዙ ወጣ ገባ ባያበዙ ማለቴ ነው። እነ ኦነግ እና አርበኞች ግንባር እንኝን ለምደዉታል። ሸርም ብለዋል። እነዛም ሸር ብለው ይሆናል። ሻብያ ታሪኩ ከዚህ ዉጭ አይደለምና።

ኦነግና ኦብነግ(ኦጋዴን ብህራዊ ነፃ አዉጭ ንባር) ከኢትዮጵያጋር ያላቸው ቅራኔ ወይም ችግር እኛ ከምናተኩራቸው ከዲሞክራሲ ጥያቄዎች ጋር አደለም። እንደነሱ እንደነሱ እንወክልሃለን የሚሉት ህዝብ  ችግር የሚፍታው ቅኝ የተያዘ ህዘብ ችግር በሚወገድበት የዲሞችራሲያዊ መብት አፈታት ስልት ነው። ይህም በአለም አቀፍ ህብረተሰብ በተደነገገ ህጋዊና

ፖለቲካዊ ቅኝ የተገዙ ህዘቦች ነፃ የመሆን መብት ነው ባዮች ናቸው። ይህ እንገዲህ የእኛን፡የዴሞክራሲ ጥያቄ፡ የዘለለ ሁናቴን ነው የሚገልፀው። ይህም የሚያሳየው የኢትዮጵያ አካል አልነበርንምና ነፃነትን ከቅኝ ግዛት እንፈልጋለን የሚለው የዲሞክራሲ፡መርሃቸው የትግላቸው የማእዘን ድንጋይ እንደሆነ ነው። ይህም በየ ድህረ ገጾቻቸውና በፖለቲካ ፕሮግራሞቻቸው የተቀመጠ ሃቅ ነው። እነሱም ክደውት አያውቁም። አንዳንድ የትንዲ አባል ቡድኖቸና ደጋፊዎች የተለየ ገጽታ ለመስጠት ቢባዝኑም እውነታውን መሸፈን አልቻሉም።

እኛ ዲሞክራሲ መብት የምንለው ከመገንጠል መለስ ያሉ ጉዳዮችን ነው እነሱ ደግሞ ዴሞክራሲ የሚሉት ከቅኝ ተገዠነት በሰላማዊ መንገድ በስምምነት ተላቆ ነፃ መንግስት መሆንን ነው። ልክ እንደሻብያ ጥያቄና ትግል መሆኑ ነው። እኛ የምናወራውን የዲሞክራሲ አስተሳሰቦችን እነሱ ነፃ መንግስት ከሆኑ በሁዋላ በሉአላዊ መንግስታቸውና ዜጋቸው መካከል የሚነሳና የሚፈታ ፅንሰ ሃሳብ ነው።እነሱ ስለ፡የእኛ አይነት ዲሞክራሲ ጥያቄ ለማውራት የሚፈላጉት ከግንጠላ በህዋላና ባሻገር ከነፃ ህዝባቸው ጋር ነው።ባጭሩ የእነዚህ ሀይሎች ፍላጎት በመጻፍ በመናገር በመሰብሰብ በቐቐንቐ መናገር ወዘተ መብቶች ጋር የተያያዘአይደለም።ስለዚህም የእነዚህ መብቶች በኢትዮጵያ መከበር ለነሱ ትርጉሙ አምብዛም ነው።እነሱ የእንግሊዝ የጣለያን የፖረቹጋል ቅኝ ገዥ ከአፍሪካ ያለምንም ቅድመሁኔታ በሰላም ወይም በጦርነት እንደወጣ ሁሉ ከኦሮሚያና ከኦጋዴን የአቢሲኒያ ቅኝ ገዥ በሰላማዊና በስምምነት መንገድ ይውጣ ባዮች ናቸው።ለዚህም ነው የተመሰረቱትና የሚታገሉት፡፡በመጀመሪያ ይህ እውነታ ከገባንና ከተቀበልን በሁዋላ ነው ስለ ትነዲ ምንነት ማወቅ የምነችለው። ከዚያም የምንመረምረው፡፡

እንደተመለከትነው ኦነግ ኢትዮጵያዊ አጀንዳ እንደሌለውና አላማውም ከቅኝ ግዛት ነፃ ማውጣት እንደሆነ ያደባባያ አቐሙ ነው፡፡ኦነግ በግንቦቱ ምረጫ አልተሳተፈም። በተቃዋሚ ድርጅቶች በኩል ለምረጫ የተሳተፉት ሃይሎች አገራዊ ኢትዮጵያዊ አጀንዳ አነግበው ነው። ህብረትም ሆነ ቅንጅት ያአገር አንድነትነ ጉዳይ ማእከል ነበር ያድርጉት። ኦነግን ዱብዳ የሆነበት እወክለዋለው የሚለው፡ህዝብ ላገራዊ አጀንዳ ሆ ብሎ ባልገመተው ሁናቴ መነሳቱና ከነዚህ ሃይሎች ጋር መሰለፉ ነው። ለዚህም ትነዲን እንደ ንብስ አድን መዳኒት ሆኖት እንደቀድሞው ኦሮሞን ብቻ ሳይሆን የአንድነት ቀናኢውንም ለአጀንዳው አጨፋሪ አድርጎ አሰልፎ እንዲመራውና እንዲገን እድሉንና መድረኩን አስገኝቶለታል። ባጭሩ የግንቦቱ ምርጫ ወያኔን ብቻ ሳይሆን ሻብያንና ኦነግን ጭምር ነው ያስደነገጠው፡፡ትነዲ የድንጋጤውም ውልደት ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አይደለም።

ይህ ፅሁፍ ታዲያ ኢትዮጵያን ዳግም ወዴት ? አፍራሹ ማነው ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ፍንጭ ይሰጣል ብዬ ነው።እኛስ አገራዊ አቐም አለን፡፡ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች ! የምንል የጥፋት መሳሪያ ሆነን መቀጠል አለብን ወይስ ፈርጥመን ትነዲንና አባል ድርጅቶቹ እራሱንና እራሳቸውን መርምረው ኢትዮጵያዊ ካባ እንዲለበሱ መጎትጎትና መታገል ?

ለማጠቃለል ትነዲ የትብብር አይነት ነው።ከነጭምልቅልቁ። የትብብር አይነት ስለሆነ ድክመቶቹን ተገንዝቦና በሽታዎቹን አክሞ የሚቀጥልበት ሁኔታ መፈለገን ይሻላል። ለዚህም በአሁኑ አቅሙ ስር ሰዶ እንዳይጉዋዝ መከታተሉና መግታቱ የግድ ነው፡፡ምክንያቱም የኢትዮጵያን ጥቅምና ልእልናን ዘላቂ የሆነ ዲሞክራሲያዊ ሰርአት ምስረታን በግልጥ አሳልፎ የሚሰጥ አቋዋም ይዞ ስለሚገኝ ነው። ይህም በመሰራች ሰነዶቹ ውስጥ ጎለቶ የተቀመጠ ገሀድ ሀቅ ነው። ይሄ ሁናቴ ካልተስተካከለ ትነዲ እድሉ አንድ ብቻ ሆኖ ይቀራል፡፡እስኪ.ቃና ድረስ ኢትዮጵያዊያኖች የሚታገሉት ስብስብ ይሆናል።